# ከወሊድ መሰረታዊ መብቶች ጋር የተያያዙ ጠቃሚ መመሪያዎች

birthrights

# ከወሊድ መሰረታዊ መብቶች ጋር የተያያዙ ጠቃሚ መመሪያዎች

የወሊድ መብቶች (Birthrights) ተዘጋጀው ይህመረጃ በእርግዝና እና በወሊድ ወቅት ሊከበሩ ስለሚገባቸው ሰብዓዊ መብቶች ጠቃሚ መረጃዎችን ይሰጣል።

እነዚህ ጠቃሚ መረጃዎች ከወሊድ ጋር የተያያዘ እንክብካቤ በሚደረግበት ወቅት ሊሟሉ ሰለ ሚገባቸውሰብዓዊ መብቶች ማብራሪያ ይሰጣሉ።

ሌሎች ጠቃሚ መመሪያዎች በእንግሊዝኛ ቋንቋ ከደህረ ገጻችን www.birthrights.org.uk ማግኘት ይቻላል።

1. **በማንኛውም ጊዜ ሰብዓዊ ክብርሽን በጠበቀ መልኩ እና በአክብሮ ትህክምና የማግኘት መብት አለሽ።**

የሰብዓዊ መብቶች ህግ፣ እንደ ሆስፒታሎች ያሉ ህዝባዊ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ሰብዓዊ ክብርሽን በጠበቀ መልኩ ህክምና እንዲሰጡ ያሰገድዳል።

የጤና ባለሙዎች (ሐኪሞች እና አዋላጅ ነርሶች) በጨዋነት እና በአክበሮት ሊይዙሽ ይገባል።

የህክምና አይነት መምረጥ እና ውሳኔ ማድረግ እንድትችይ የመደገፍ ኃላፊነት አለባቸው።

ስለ አንቺ ወይም ስለምትፈልጊው ህክምና በግምት ድምዳሜ ማድረግ አይገባቸውም።

ክትትል የሚያደርጉልሽ የጤና ባለሙያዎች መከታተል የምትፈልጊውን የህክምና አይነት መወሰን እንድትችይ፣ አሰተርጓሚ ካሰፈለገሽ አሰተርጓሚ ማግኘትሽን ማረጋገጥ ይገባቸዋል።

ብቻሽን መሆን በፈለግሽባቸው ጊዜያት ሁሉ ይህ መብትሽ ሊከበር ይገባል፤ ለምሳሌ በምጥ ወቅት ወይም በምታጠቢበት ወቅት ብቻሽን የመሆን መብት አለሽ።

ሌሎች የምትፈልጊያቸው የተለዩ ፍላጎቶች ካሉ በተቻለ መጠን ይህ ፍላጎትሽ ሊከበር ይገባል፤ ለምሳሌ መታከም የምትፈልጊው በሴት የህክምና ባለሞያዎች ብቻ ከሆነ እና ይህ የሚቻል ከሆነ ይህ ፍላጎትሽ ሊከበር ይገባል፤ ይሁንና ህክምና የሚሰጡት ባለሞያዎች ወንዶች ብቻ ከሆኑ እና በምጥ ወቅት የህመም ማስታገሻ ቢያስፈልግሽ ውሳኔ ማድረግ እንድትችይ የሚያስፈልጉት መረጃዎች ሁሉ ሊነገርሽ ይገባል።

አንድ አይነት የአካል ጉዳት እክል ወይም ለረዥም ጊዜ የዘለቀ የጤና ችግር ካላብሽ ክትትል የሚደርጉልሽ የጤና ባለሙያዎች ከሌላው ሰው እኩል የምትፈልጊውን ህክምና ማግኘትሽ እርግጠኛ መሆን አለባቸው። ይህም ከሌላው የተለየ ወይም ተጨማሪ እንክብካቤ እና የሚያስፈልግሽን ድጋፍ ማደረግ ያካትታል። (ለምሳሌ የአካል ጉዳት ላለባቸው ሰዎች ተለይተው የተዘጋጁ መጸዳጃ ቤቶች መጠቀም እንድትችይ ማደረግ፣ ልጅ ከወለድሽ በኋላ ተጨማሪ ድጋፍ እንዲደረግልሽ ማደረግ ወይም ድምፅ የሚረብሽሽ ከሆነ በተቻለ መጠን ፀጥታ የሰፈነበት ቦታ እንድታረፊ ማድረግ)።

## 2. አንድን የህክምና አይነት ‘አልፈልግም’ የማለት መብት አለሽ።

ልክ እንደ ሌላው ወቅት ሁሉ በእርግዝናሽ ወቅትም ከገዛ አካልሽ ጋር በተያያዘ የፈለግሽውን ውሳኔ የማድረግ መብት አለሽ።

የጤና ባለሙያዎች አንድ አይነትህክምና ከማድረጋቸው በፊት መስማማትሽን (ይሁንታሽን) በቅድሚያ ሊጠይቁ ይገባል።

ለምሳሌ ምርመራ ከማደረጋቸው በፊት፣ የደም ግፊትሽንከመለካታቸው በፊት እና የህመም ማስታገሻ ከመሰጠታቸው በፊት መስማማትሽን (ይሁንታሽን) መጠየቅ እንደሚገባቸው ህጉ ይደነግጋል።

አንቺ ሳትስማሚ ህክምና መስጠት ከህጉ ጋር የሚጋጭ ድርጊት ነው።

አንድን የህክምና አይነት በማንኛውም ጊዜ ‘አልፈልግም’ የማለት መብት አለሽ፤ ይህ በፈቃደኝነት አለመስማማት (ይሁንታ አለመስጠት) ይባላል።

አንድን የህክምና አይነት ፈልገሽ ከተስማማሽ (‘እሺ’ ካልሽ) ይህ ይሁንታ መስጠት (መስማማት) ይባላል።

ውሳኔ ለማድረግ ተጨማሪ ጊዜ ካሰፈለገሽ ይህንን መጠየቅ ትችያለሽ።

በፈቃደኝነትተስማማሽበት የነበረን ህክምና ከጊዜ በኋላ መቀየር ትችያለሽ።

የጤና ባለሙያዎች ከአካልሽ ጋር በተያያዘ ባደረግሽው ውሳኔ ባይስማሙምእንኳ ውሳኔሽን ሊያከብሩልሽ ይገባል።

በህጉመሰረትይሁንታሽ (መስማማትሽ) ትክክለኛ መሆን ይገባዋል፤ ይህም ለመከታተል የመረጥሽውንየህክምናአይነት በበቂ ሁኔታ ተረድተሽ የወሰንሽው መሆን ይገባዋል፤ ለውሳኔ እንዲረዳሽ የሚሰጥሽ መረጃ መረዳት በምትችይው መንገድአንዲሁምህክምናውን መከታተል ያለውን አደጋ እና ለአንቺ ያለውን ጥቅሞች ግልጽ በሆነ መንገድ የሚያስቀምጥ ሊሆን ይገባል።

የቤተሰብ አባላት ወይም የጤና ባለሙያዎችን ጨምሮ ማንም ሰው አንድን አይነትህክምናእንድትከታተይ ጫና ሊያሳድርብሽ ወይም ሊያስገድድሽ አይገባም፤ ከወሊድ ጋር በተያያዘ የወሰንሽውን ውሳኔ ብቻ መሰረትበማደረግየማህበራዊ ጉዳይ አገልግሎት ጉዳዩ እንዲያውቀው አይደረግም።

በህጉመሰረትያልተወለደህፃን መብት የለውም። ይህ ማለት የጤና ባለሙያዎች አንድንአይነትህክምናላልተወለደው ልጅ እንደሚጠቅመው ቢያስቡ እንኳ በእርግዝና ወቅት እና በወሊድ ጊዜአንቺ ያልተስማማሽበትንህክምና ሊሰጡሽ አይችሉም፤ የህክምና ባለሙያዎች ከሚሰጡት ምክር በተቃራኒ የመምረጥ ነፃነት አለሽ።

ብዙ ጊዜ ባያጋጥምም ሌሎች ሰዎች አንቺን ወክለው ውሳኔ ሊያደርጉ የሚችሉበት ብቸኛ ወቅት በራስሽ መወሰን የማትችይበት ስነ-አዕምሮአዊ ሁኔታ ውስጥ ስትሆኚ ነው፤ አንዲህ አይነት ሁኔታ ሲያጋጥም ሌሎች (ለምሳሌ ሐኪሞችሽ) ለአንቺ የሚበጀውን ውሳኔ ለመወሰን ስነ-አዕምሮአዊ ብቃት ህግ (Mental Capacity Act) የተቀመጡ ህጋዊ ሂደቶችን የመከተል ግዴታ አለባቸው።

## 3. ለእናትና ለልጅ የሚደረግ እንክብካቤ በቂ ምክንያት እስከሌለ ደረስ በጎ ምላሽ ሊቸረው ይገባል።

አገልግሎት ለማግኘት የሚቀርቡ ጥያቄዎች በእንክብካቤ ሰጪው ተቋም አዎንታዊ ምላሽ ሊሰጣቸው ይገባል፤ የአንቺን ፍላጎት ለማሟላት የተቻላቸውን ጥረት ሊያደርጉ ይገባል።

እንክብካቤ በሚደረግበት ወቅት ተስማሚ የሆነውን እንክብካቤ የመምረጥ መብት አለሽ፤ ለምሳሌ የምትወልጂበትን ቦታ (ይህም በጤና ተቋማት፣በአዋላጅ ነርሶች ማዋለጃ ማዕከላት ወይም በቤት ሊሆን ይችላል) የመምረጥ መብት አለሽ፤ እንዲሁም በቀዶ ህክምና ለመውለድ ከፈለግሽ ይህ መብት ሊከበርልሽ ይገባል።

አንዳንድ ጊዜ አንድን ጉዳይ አስመልክቶ  የራስሽን ምርጫ ማድረግን በተመለከተ ገደቦች ይኖራሉ። ለምሳሌ የማዋለጃ ማዕከላት በማዕከሉ መውለድ የሚችሉት እነማን እንደሆኑ፣ ወይም ሆስፒታሎች ገንዳ ውስጥ የመውለድ አገልግሎት ማግኘት የሚችሉት እነማን እንደሆኑ መመሪያ ሊኖራቸው ይችላል፤ እነዚህ መመሪያዎች ህጋዊ ደንቦች አይደሉም።

ከወሊድ ጋር የተያያዘ የእንክብካቤ አገልግሎት በምትጠይቂበት ወቅት የምትፈልጊውን እንክበካቤ ለመስጠት ጥረት ሊያደረጉ ይገባል፤ ይሁንና የተጠየቀውን የህክምና (እንክበካቤ) አይነት ጉዳት በማያደርስ መልኩ መስጠት አዳጋች ከሆነ የተጠየቀውን ህክምና ላለመስጠት እንክብካቤ ሰጪው ተቋም እምቢ ሊል ይችላል።

ያለሽበትን ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት ውሳኔ ሊያደረጉና ውሳኔ ያደረጉበትን ምክንያትም ሊያስረዱሽ ይገባል፤ ምክንያቱን ሲገልጹ ፖሊሲው ወይም መመሪያው አይፈቅድም አንደሚሉት ያሉ ምላሾች በቂ አይደሉም።

ከመውለድ ጋር ተያይዞ ሁልጊዜ ልትመርጫቸው የምትችያቸው ምርጫዎች አሉ፤ ለምሳሌ በቤትሽ ውስጥ መውለድ ከፈለግሽ ማንም ሰው ወደ ሆስፒታል አንድትሄጂ ሊያስገድድሽ አይችልም፤ እንዲሁም ያለ አዋላጅ ነርሶች ወይም ሐኪሞች እርዳታ የመውለድ ህጋዊ መብት አለሽ።

የምትፈልጊውንየህክምናአይነትካላገኘሽ እንደሁም ፍላጎትሽ ካልተከበረ የአዋላጅ ነርሶችን ኃላፊ (Head of Midwifery) (senior midwife) ለማነጋገር ልትጠይቂ ትችያለሽ፤ አንዲሁም Birthrights የተባለውን ድርጅት በኢሜይል፡ advice@birthrights.org.uk ምክር መጠየቅ ትችያለሽ።

## 4. ሁሉም መሰረታዊ ፍላጎቶችሽ እንዲሟሉ የመጠየቅ መብት አለሽ።

ሆስፒታል ውስጥ ከሆንሽ የሚያሰፈልጉሽ መሰረታዊ ነገሮች ማለትም እንደ ምግብ፣ ውሃ፣ ህመም ማስታገሻ እና ወደ መጸዳጃ ቤት ለመሄድ የሚያስፈልግ ድጋፍ ሊሟላልሽ ይገባል።

እርዳታ ወይም እንክብካቤ አስፈልጎሽ የምታቀበርቢያቸው ጥቄዎች በሙሉ በቁም ነገር ሊታዩ እና አፋጣኝ ምላሽ ሊያገኙ ይገባል።

በምጥ ወቅት የህመም ማስታገሻ ብትጠይቂ እና ከጤናሽ አንጻር ጉዳት እንደሚያስከትል በቂ የሆነ ምክንያት ከሌለ በስተቀር የህመም ማስታገሻ ሊሰጥሽ ይገባል፤ በቂ ምክኒያት ካለ ግን ሐኪምሽ ወይም አዋላጅ ነርሷ የህመም ማስታገሻ መስጠት የማይቻልበትን ምክንያት ሊያስረዱሽ አንዲሁም ውይይቱን መዝግበው በሰነድ ሊይዙ ይገባል።

እርዳታ ወይም እንክብካቤ አስፈልጎሽ የምታቀበርቢያቸው ጥያቄዎች እንዳልተሰሙ ከተሰማሽ ከህክምና ክፍሉ ሐኪም ወይም የአዋላጅ ነርሶች ኃላፊዋን ለማነጋገር ልትጠይቂ ትችያለሽ።

## 5. በወሊድ ወቅት የሌሎችን ድጋፍ የማግኘት እና ከቤተሰቦችሽ ጋር የመሆን መብት አለሽ።

የሰብዓዊ መብቶች ህግ የምትወልጂበትን ቦታና የምትወልጂበትን መንገድ የመወሰን አንዲሁም ስትወልጂ ማን አብሮሽ እንዲሆን አንደምትፈልጊ የመወሰን እና የመምረጥ መብት ይሰጣል።

በምጥ ወቅት አብሮሽ እንዲሆን የምትፈልጊውን ሰው የመምረጥ መብት ሊኖርሽ ይገባል። የጤና ተቋማት(ሆስፒታሎች) እና የማዋለጃ ማዕከላት በወሊድ ወቅት ምን ያህል ሰው አበሮሽ መሆን እንደሚችል የሚወስኑ እንዲሁም ልጆች አብረው መቆየት እንደማይችሉ የሚገልፁ ፖሊሲዎች ሊኖሯቸው ይችላሉ፤ ይሁን እንጂ አነዚህ የሆስፒታል መመሪያዎች እንጂ ህጋዊ ደንቦች አይደሉም፤ ያሳሰቡሽን ጉዳዮች አስመልክቶ አዋላጅ ነርስሽን ማነጋገር ወይንም የአዋላጅ ነርሶቹን ኃላፊ ለማናገር ልትጠይቂ ትችያለሽ።

በምጥ ወቅት ወይም ከወለድሽ በኋላ ልታይው የማትፈልጊው ሰው ካለ ለአዋላጅ ነርስሽ ልትነግሪያት ትችያለሽ።

## 6. ቅሬታ የማቅረብ መብት አለሽ።

ህክምና እና እንክብካቤ በምታገኚበት ጊዜ ሁሉ ሰብዓዊ ክብርሽን በጠበቀ መልኩ እና በአክብሮት ህክምና የማግኘት መብት አለሽ።

በእርግዝና ወቅት የሚደረግልሽ ህክምና የሚያሳስብሽ (የሚያስጨንቅሽ) ከሆነ አዋላጅ ነርስሽን ወይም ሀኪምሽን ወይም የአዋላጅ ነርሶቹን ኃላፊ (Head of Midwifery) (senior midwife) ብእምነት (Trust) ልታነጋግሪ ትችያለሽ።

በሰጡሽ መልስ ካልተደሰትሽ ወይም ሰብዓዊ ክብርሽን በጠበቀ መልኩ እና በአክብሮት ህክምና ካላገኘሽ ቅሬታ ማቅረብ ትችያለሽ፤ ያን ያህል የጎላ ስህተት ተፈፅሞ ባይሆንም ወይም የከፋ ጉዳት ባያደርስም እንኳ ቅሬታ ማቅረብ ትችያለሽ።

በሆስፒታል ውስጥ የሚገኘው የህሙማን አማካሪና አገግልግሎት (Patient Advice and Liaison Service) (PALS) የተባለው ቡድን (የሥራ ክፍል) ቅሬታሽን ማቅረብ እንድትችይ ይረዳሻል።

በሰጡሽ ምላሽ ካልተደሰትሽ ቅሬታሽን ወደ እንባ ጠባቂ ተቋም መውሰድ ትችያለሽ።

Birthrights የተባለው ድርጀትም ከወሊድ ጋር በተያያዘ ያሉሽን መብቶችን እና ቅሬታሽን ማቅረብ የምትችይበትን መንገድ በተመለከተ በነፃ ያማክራል፤ Birthrights በ advice@birthrights.org.uk. የኢሜይል አድራሻ አማካኝነት መጠየቅ ትችያለሽ።

## 7. በማንኛውም ጊዜ ህክምና የማግኘት መብት አለሽ።

በዩናይትድ ኪንግደም (እንግሊዝ) ጊዜያዊ ነዋሪዎች የሆኑ ሰዎች ሁሉ ከአሃገሪቱ ብሔራዊ የጤና አገልግሎት (NHS) በነፃ የህክምና አገልግሎት የማግኘት መብት አላቸው፤ የአገሩ ጊዜያዊ ነዋሪ ያልሆኑ ሰዎች ለሚያገኙት ህክምና መክፈል ሊኖርባቸው ይችላል።

ይሁንና ህክምና ለማገኘት መክፈል ቢኖርብሽና መክፈል ባትችይ እንኳ ከወሊድ እንክበካቤ እና ህክምና ጋር በተያያዘ መክፈል እስክትችይ ሳይጠበቅ ህክምና ሊሰጥሽ ይገባል።

ማን መክፈል እንዳለበት እና አከፋፈሉ እንዴት እንደሚሆን የሚደነግጉት መመሪያዎች እጅግ ውስበስብ ናቸው። ከወሊድ እንክበካቤ ጋር በተያያዘ መክፈል ይገባሽ እንደሆነ የሚያሳስብሽ ከሆነ Maternity Action የተባለ ዕርዳታ ድርጅት ሊረዳሽ ይችላል፤ ድርጅቱ በቀጥታ (Online) መረጃ ይሰጣል፤ እንዲሁም በኢሜይል እና  በስልክ ነፃ የምክር አገልግሎት እና የማስተርጎም አገልግሎት ይሰጣል።

ማስተባበያ: የእኛ በራሪ ወረቀቶች በእንግሊዝ ውስጥ ስለ ሕጉ መረጃ ይሰጣሉ። መረጃው በተጻፈበት ጊዜ *(May 2021)* ትክክል ነው ። በዚህ አካባቢ ያለው ሕግ ሊለወጥ ይችላል ። በሕጉ ላይ የተደረጉ ለውጦች ከዚህ ህትመት ጊዜ ያለፈባቸው ከሆነ *Birthrights* ተጠያቂ ሊሆን  አይችልም ። *Birthrights* በዚህ በራሪ  ወረቀት ላይ ባለው መረጃ ላይ በመመርኮዝ ለሚነሳ ኪሳራ ምንም ዓይነት ኃላፊነት አይቀበልም። የ*Birthrights* ለሶስተኛ ወገን *www.birthrights.org.uk* አቅርቧል ፣ እነዚህም ተዛማጅ ተጨማሪ መረጃዎችን ለማቅረብ ይረዳሉ ። የ*Birthrights* ለተገናኙ *website* ይዘቶች ምንም ኃላፊነት አይወስድም እናም *link* እንደ ማረጋገጫ ሊወሰዱ አይገባም።